# ኢትዮጵያን ማን ይምራት?

**ከዮሐንስ**

አገራችን ኢትዮጵያ 4ኛውን ብሔራዊ ምርጫ ለማካሄድ በዝግጅት ላይ እንደሆነች ይታወቃል። ስለ ምርጫ ሲነሳም መራጮችና ተመራጮች የተመለከቱ ውይይቶች መደረጋቸው አይቀርም ። መራጮችና ተመራጮችን በተመለከተ በርካታ ርእሰ ጉዳዮች ተነስተው ውይይት ሊደረግባቸው የሚችል ቢሆንም በዚህች አጭር ጽሑፌ የማተኩረው ተመራጮች ወይም የነገ መሪዎቻችን በተመለከተ ይሆናል።

አገራችን ኢትዮጵያ ማን ይምራት ወይም እኛ የኢትዮጵያ ሕዝቦች ማን ይምራን ወደሚለው ከመግባቴ በፊት ግን የነገ መሪዎች (ፖለቲከኞች) ሊያወጡ ስለሚችሉት ስብስቦች ወይም የፖለቲካ ፓርቲዎች ጥቂት ልበል።

በአጼዎቹ ዘመናት ሕጋዊ ሰውነት ያላቸው የፖለቲካ ስብስቦች እንዲኖሩ የሚያስችል አሰራርም ሆነ የሕግ መሰረቶች ስላልነበሩ ትኩረቴ ከደርግ ጊዜ በኃላ በተፈጠሩት (በታዩት) ልዩ ልዩ ስብስቦች ላይ ይሆናል።

የአጼ ኃይለስላሴ አገዛዝ ተቃውመው ወደ ሽምቅ ውጊያ የተሰማሩ በርካታ ስብስቦች እነደነበሩ ሁሉ፤ የአጼው አገዛዝ ወድቆ ደርግ በትረ ስልጣኑን ሲጨብጥ የተሻለ የፖለቲካ እና ዴሞክራታይዜሽን ሂደት ይኖራል ብለው ፓርቲ ያቋቋሙ ግለሰቦች( ስብስቦችም) ነበሩ። በደርግ በተለይ ደግሞ በሊቀመንበር መንግስቱ ለታይታ (ለይስሙላ) ሲፈጠሩ፤ ሲቀላቀሉ ፤ ስም ሲቀይሩ ወይም እስከወድያኛው ሲከስሙ የታዩ ፓርቲዎችም ነበሩ።

በከተማ ውስጥ ሆነው«ሰላማዊ» ትግል ሲያካሂዱ ከነበሩት ፓርቲዎች መካከል ጥቂቶቹን ለመጥቀስ ያህል:- መኢሶን፤ ኢሕአፓ፤ ወዝሊግ፤ ኢጭአት፤ማሌሪድ፤አብዮታዊ ሰደድ፤ ኢማሌድኅ ወዘተ ይገኙበታል። አሁን ያሉት የፖለቲካ ፓርቲ መሪዎች አብዛኛዎቹ ይነስም ይብዛ ወይ አገዛዙን ተቃውመው በረሃ የወጡ  ወይም በከተማ ውስጥ የነበሩት ፓርቲዎች አይድዮሎጂ የተቀበሉ ነበሩ ለማለት ይቻላል።

እንደሚታወቀው ከዝቅተኛ የጦር ሹሞች ተውጣጥተው የጦር ሰራዊቱን አቤቱታ ለማስማት የተመረጡት መኮንኖች በሊቀመንበሩ እስስታም አካሄድ ከተወገዱ(እርምጃ ከተወሰደባቸው) በኃላ ሊቀመንበሩ ሙሉ በሙሉ አምባገነን ሆኑ ። እንኳን ተቃዋሚ የፖለቲካ ፓርቲ ሊኖር ይቅርና በግለሰብ ደረጃም የነበረው አገዛዝ የሚቃወም ማንኛውም ዓይነት ሃሳብ ወይም ንግግር ላቀረበ «የፍየል ወጠጤ» ይዘፈንበት እንደነበርም የቅርብ ጊዜ ታሪካችን ነው። በአምባገነናዊው አገዛዝ የተነሳም አገራችን በታሪክዋ አይታው የማታውቅ የኢኮኖሚ፤የሰውና የንብረት ውድመት ደረሰባት ።

ከዚህ በኃላ ኢ.ህ.አ.ዴ.ግ. በ1985 ዓ.ም የፌዴራላዊ ሕገ መንግስት ካጸደቀ በኃላ አገራዊና ክልላዊ የፖለቲካ ፓርቲዎች እንደ አሸን እንደፈሉ አይተናል።

በ1997 ዓ.ም ለተደረገው የምርጫ ዝግጅት 11 አገር አቀፍ እና 56 የክልል ባጠቃላይ 67 የፖለቲካ ፓርቲዎች ሕጋዊ ሰውነት ማረጋገጫ ወረቀት ተሰጥቷቸዋል።በ 2002 ዓ.ም ለሚደረገው ምርጫ ከ 100 የማያንሱ የፖለቲካ ፓርቲዎች እንደሚሳተፉ ይጠበቃል።

ይህ የሚያሳየው ህዝቡ በየደረጃው በመሰባሰብ የመብቱ ተሟጋች ሊሆኑት የሚችሉ ድርጅቶች ማቋቋም መቻሉን እና በአገራችን አዎንታዊ እና ተስፋ ሰጪ የዴሞክራሲ ሂደት መኖሩን ነው።

የፖለቲካ ፓርቲዎች መቋቋማቸው በአዎንታዊ ጎኑ የሚታይ ሆኖ እነዚህ ፓርቲዎች ሲጀመርም የ ያገባኛል ባዮች (Stake Holders) ተወካዮች እንደመሆናቸው ከግለሰባዊ አስተሳሰብ ተላቅቀው የቡድን ጥቅም ሊያስጠብቁ የሚችሉ ተግባራት ማከናወን ቀዳሚ ተግባራቸው ማድረግ አለባቸው ።

በክልልም ሆነ በአገር አቀፍ ደረጃ እነዚህ ቡድኖች የበላይነት አግኝተው ህዝቡን የማስተዳደር እድል ሲያገኙ የሚያገለግሉት ለደገፋቸው ወገን ብቻ ሳይሆን ላልደገፋቸውም ጭምር እንደሆነ የፖለቲካ ሀሁ ያስተምረናል፡፡

ባለፈው ምርጫ በተግባር ያየነው ግን ይህን የሚያሳይ አይደለም ገና ለገና የአንድ ክልል ድምጽ እናገኛለን በሚል ስሌት «ዕቃ ወደ ቀበሌ .........» ብለው ነበር፡፡ በዚህም አላበቁም በያዝነው ክፍለ ዘመን የሽምቅ ውጊያ ፋሽኑ ያለፈበት ስለሆነ ሰውም ሳይሞት፤ንብረትም ሳይወድም መብታችሁ ሁሉ ተጠብቆላችሁ ሰላማዊ ትግል ታገሉ ላላቸው መንግስት «ወደ ዱር እንመልሰዋለን» ብለው በአደባባይ አወጁ፡፡ አገራችን ያሉዋት ተቃዋሚዎች እንዲህ የሚያስቡ ናቸው፡፡

በሌላ በኩል ክልልም ሆነ አገር ለመምራት የሚዘጋጁ ግለሰቦች በየቡድናቸው የሚያሳዩት ባህሪያት፤የአመራር ብቃትና አስተሳሰባቸው ጤነኛ አመራር ለመስጠት የሚያስችሉ ወሳኝ መስፈርቶች ናቸው፡፡አንድ ግለሰብ በሚመራው ቡድን ውስጥ ከእኔ ውጪ...... የሚል አስተሳሰብ ካለው ፤ የአባላቱን አስተያየት ተቀብሎ የማያስተናግድ ከሆነ ፤ ችግሮች በመቻቻል እንጂ በመካረር ሊፈቱ እንደማይችሉ የማያምን ከሆነ ባጠቃላይ ባህርዩ አምባገነን ከሆነ ለበለጠ አገራዊና ክልላዊ ኃላፊነቶች ሲበቃም ህዝቡንና አገሪቱን ጤና ባለው አመራር ሊመራ ይችላል ብሎ ማሰብ የዋህነት ነው፡፡ያልነበረ ባህሪይ በአንድ ጊዜ ሊበቅል አይችልምና፡፡

ከዚህ በመነሳት በተለይ አገር አቀፍ ተብለው የተቋቋሙ ስብስቦች(ፓርቲዎች)የአገሪቱን ሕገ መንግስት በማክበር ፤ የሕግ የበላይነትን በመቀበል ጤናማ የፖለቲካ ውድድር ማድረግ ለራሳቸው በተለይ ደግሞ ለሃገራችንና ለሚመሩት ህዝብ የጎላ ጠቀሜታ እንዳለው መረዳት መቻል አለባቸው፡፡

በተጨባጭ በአገራችን እየታየ ያለው እውነታ ግን ከዚህ በእጅጉ የተለየ ነው፡፡ ሲጀምር የፖለቲካ ፓርቲዎቹ ሲቋቋሙ የዓላማቸው አልፋና ኦሜጋ በስልጣን ላይ ያለውን ፓርቲ ማስወገድ ነው ፡፡ በስልጣን ካለው ፓርቲ በተሻለ ሁኔታ አገሪቱን ሊያበለጽግ የሚችል ፖሊሲ እና ስትራተጂ ይዘው ከቀረቡ በርካታ ደጋፊ ሊያገኙ እንደሚችሉ ጥርጥር የለውም፡፡ነገር ግን አንዱ ተቃዋሚ ፓርቲ መሪ ባንድ ወቅት በፓርላማ እንደተናገሩት «የተቃዋሚዎች ሚና መቃወም » ሆነና ነገር ዓለሙ ሁሉ ተበላሸ፡፡

ገዢ ፓርቲው ስልጣን ከመያዙ በፊት የነበሩት የትምህርት አቅርቦቶችና በአሁኑ ጊዜ ያለው አጠቃላይ የትምህርት ሽፋን፤በአገሪቱ ያለው የጤና ሽፋን፤የኤሌክትሪክ፤የውሃና መገናኛ ስርጭት፤ መንገድና ሌሎች መሰረተ ልማቶች የሚታዩና የሚዳሰሱ ሆነው ተሰርተው እያሉ«ዋና ሚናቸው መቃወም ስለሆነ የለም አይናችን ግንባር ያድርገው» የሚሉ ከሆነ ይህንን ሃቅ በአይኑ እያየና በተግባር እየተጠቀመበት ያለው ሕዝብ እንዴት ይመርጠናል ብለው ያስባሉ? መራጩ የሚደግፉትና የሚቃወሙትን ለይተው የማያውቁ፤ ውሸታሞች እና ጭፍን መሪዎች ከመረጠ ነገ ምን ዓይነት ሁኔታ ሊያጋጥመው እንደሚችል በሚገባ የሚገነዘብ ይመስለኛል፡፡

በተያያዘ መልኩ አንድ የፖለቲካ ድርጅት አገርን የሚያህል የአመራር ኃላፊነት ከመውሰዱ በፊት መጀመርያ የትልቁ ፖለቲካ መድረክ አምሳል የሆነውን ትንሹ ፓርቲውን አጥርቶ፤አጠንክሮ መውጣት የግድ ይለዋል፡፡ አሁንም ከግለሰብ አንጻር ሳይሆን ድርጅቱ ካስቀመጣቸው ዓላማዎች አንጻር አመራሩን ማብቃትና ችግሮች ሲኖሩም በውይይት የመፍታት ባህል ሊያዳብር ይገባል፡፡

በአገራችን ያሉ አካሄዶች ግን ከዚህ በእጅጉ የራቁ ሆነው እናያቸውለን፡፡በየቀኑ እንደምንሰማው እገሌ እና እገሌ ፓርቲዎች ተዋሃዱ ይባልና አንድ ሳምንት ሳያስቆጥሩ የጥምር ፓርቲው አባላት ንትርክ ይጀምራሉ፡፡ መድረኩ ስለጠበበ አይመስለኝም፤ ውጥረቱ ሁሉም የወንበር ፍላጎት ስለተጠናወታቸው ይመስለኛል፡፡የተጣመሩት ፓርቲዎች ሁሉም ዋናውን ወንበር የሚፈልጉት ከሆነ መቼውም ሊስማሙ አይችሉም፡፡ ወንበሩ አንድ ነዋ፡፡

በሌላ ጊዜ ደግሞ እንትና ፓርቲ ለሁለት እንደተከፈለ ይሰማል፡፡እህሳ ሲባል በስልጣን ላይ ያለው ፓርቲ ሰርጎ ገቦች አስገባበት ይባላል፡፡እንዴ! ከሰርጎ ገቦች ራሱን መከላከል ያልቻለ ፓርቲ እንዴት ነው የአገር መሪነት ቦታ ካልተሰጠኝ የሚለው? እግዚሔር ያሳያችሁ ጠላቴ ነው ብሉ ከፈረጀው ወገን የሚያጋጥመውን ሰርጎ ገብነት መቀልበስ ካልቻለ እንደ አገራችን ለመሳሰሉት ከብዙ

ምክንያቶች አኳያ በሰሜን ሲጠበቁ በምዕራብ ጠላቶች ለሚበዙባት አገር ካልመራን ብለው እንዴት አምባጓሮ ይፈጥራሉ?

ኢትዮጵያ ሁሉን አቀፍ ሕገ መንግስት ካጸደቀች ጀምሮ ተመሰረቱ ሲባል ከሰማናቸው የፖለቲካ ፓርቲዎች ውስጥ እንደጀመረ ያለ ፓርቲ ቢኖር ገዢው ፓርቲ ኢህአዴግ ብቻ ነው፡፡ሌሎቹ በሙሉ ቢያንስ ከሶስት ቦታ በላይ ተሰነጣጥቀው ሌላ ስም ወጥቶላቸዋል፡፡ታድያ እንዲህ አይነት ባህርይ ያለው የፖለቲካ ቡድን እንዴት ነው አገር የሚመራው?

## ታድያ ማን ይምራን?

እገሌ ይምራን ወደሚለው ውሳኔ ለመድረስ ገዢው ፓርቲ እና ተቃዋሚዎችን በማነጻጸር የተወሰኑ ነጥቦች ላስቀምጥ ፡-

- አንድ በማንኛውም ዓላማ የተሰባሰበ ቡድን የሚመራ አመራር(ፓርቲ) ግቡን ለመምታት ዓላማውን ማጥራት፤ ግቡን ለመምታት የሚያስችሉት መርሆች፤ፖሊሲዎች እና ስትራተጂዎች ማስቀመጥ በትንሹ የሚጠበቁ ተግባራት ናቸው ፡፡ ማንኛውም ስብስብ ቢያንስ እነዚህን ማስቀመጥ ካልቻለ የሚሰራው ስራ በነሲብ(በደመነፍስ) እንደሆነና የፈለገውን ጉልበትና ገንዘብ ቢያፈስም አንዳንድ ለምልክት የሚሆኑ ተግባራት ያከናውን እንደሆነ እንጂ ግብ መምታት የሚባል ነገር ማሰብ በፍጹም እንደማይቻል በርግጠኝነት መናገር ይቻላል ፡፡ ከዚህ አንጻር ገዢው ፓርቲ የተማረውም ሆነ ያልተማረ ኢትዮጵያዊ ሊገባው በሚችል ቋንቋ ዓላማውን አስቀምጧል ፡፡ «አገራችን በሚቀጥሉት 30 እና 40 ዓመታት መካከለኛ ገቢ ካላቸው አገራት ተርታ ውስጥ ማሰለፍ» በቃ ፡፡ ይህንን ለማስፈጸም ደግሞ ቢያንስ 4 ዋና ዋና ፖሊሲዎችና ስትራተጂዎች ቀይሷል ፡፡

    1. የግብርናና ገጠር ልማት ስትራተጂ፤
    2. የኢንዱስትሪ ልማት ስትራተጂ፤
    3. የትምህርት ስትራተጂ፤
    4. የጤና ስትራተጂ፤

የእነዚህ ስትራተጂዎች ዝርዝር በዚህች አጭር ጽሑፍ ማስፈር አልችልም ፡፡ እያንዳንዱ ስትራተጂ ራሱን የቻለ መጽሐፍ ስለሆነም እዚህ መዘርዘሩ ተገቢ አይሆንም ፡፡እያንዳንዱ ስትራተጂ ከየት ተነስቶ የት እንደሚደርስ ጥርት ባለ አገባብ እና ማንኛውም ሰው በቀላሉ ሊረዳው በሚችል መልኩ እንደተቀመጠ ሳልገልጽ ባልፍ ግን ትዝብት ይሆንብኛል ፡፡ በሽልፍ እንደሚወረወሩ በርካታ ጽሁፎች ተጽፎ አልተወረወረም በነዚሁ ስትራተጂዎች መሰረት ስራ እየተሰራ ነው ፡፡ አገራችን በተከታታይ እያስመዘገበች ያለችው እድገትና የኢኮኖሚ ለውጥም የነዚህ ስትራተጂዎች ውጤት ነው ፡፡

በአንጻሩ ተቃዋሚዎች ለስብሰባ የሚቀርብ የንግግር ጽሁፍ ካልሆነ በስተቀር አገርን ለመምራት የሚያስችል፤የዜጎችን አኗኗር የሚለውጥ ፖሊሲና ስትራተጂ ሲያቀርቡ አላየሁም አልሰማሁምም ፡፡

ሌላው አንድ አገርን ለመምራት የተሰባሰበ ቡድን ከግለሰቦች የግል ጥላቻና የወንበር ፍላጎት ባለፈ አገርና ሕዝብን ማስቀደም እንዳለበት እና ፈታኝ ሁኔታዎች ቢገጥሙትም በውይይት የመፍታትና የማለፍ ችሎታ ሊኖረው እንደሚገባ ከላይ ገልጫለሁ ፡፡ አገር በማስተዳደር ላይ ያለው ፓርቲ አባል የሆነው ሕወሐት አመራር አባላት በ 1994 ዓ.ም ለሁለት ተከፈሉ፤በነሱ ብቻ ሳይሆን ወደ ሌሎቹ የኢህአዴግ አባል ድርጅቶች የመዛመት ሽታ አሳይቶ እንደነበርም ተደምጧል ፡፡ ያን ያህል ከባድ ክፍፍል ታልፎ ግን አገርም አልተረበሸ፤መንግስትም አልፈረሰ በውይይት የተመለሱት ተመልሰው ያለፈለጉት ደግሞ ግማሹ ሰላማዊ ኑሮውን ሲመራ የተቀረው በሌላ የፖለቲካ ፓርቲ ተጠልሎ በመታገል ላይ ይገኛል ፡፡ ያልተስማሙ ግለሰቦች ወጡ ነገር ግን ገዢው ፓርቲ እንደ ፓርቲ አልተከፋፈለም መሪዎቹ እርስ በርሳቸው አልተናከሱም ፡፡ ይህ የአንድ ፓርቲ ስልጣኔ ምልክት ነው ፡፡

በአንጻሩ ተቃዋሚዎቹ የ1997 ዓ.ም ብሔራዊ ምርጫ ለማሸነፍ ህብረት መፍጠራቸው ይታወቃል ። ለገዢው ፓርቲ እንደዋና ተቀናቃኝ መስለው በመቅረባቸውም በአገራችን ጥሩ የምርጫ ፉክክር እናያለን ብለን ተስፋ አደረግን ። ልክ የአዲስ አበባ መራጭ ይሁንታ አግኝተው በአዲስ አበባ ማሸነፋቸው ሲታወቅ በዴሞክራሲ ያገኝዋትን የአንድ አከባቢ መራጭ ይሁንታ ኢ-ዴሞክራሲ በሆነ መንገድ ባልመረጣቸውም ላይ ለመጫን አሰቡ ። አስበውም አልቀሩ ትልቅ ውሸት ዋሽተው ሕዝቡን ማደናበር መተኪያ የሌለው አማራጭ ሆኖ ስላገኙት ይህንኑ አደረጉ ። እናም ረብሻ አስነሱ ። ወትሮውም ረብሻው የተጀመረው በውሸት ስለነበር ረብሻው በውሸት መጀመሩን ሲታወቅ ወድያው ቀዘቀዘ ። ልክ ይህ የጨቅላ አስተሳሰባቸው መክሸፉን እንደተረዱ መሪዎቹ እርስበርሳቸው መነታረክ ጀመሩ ። በመነታረክ አላበቁም የተወሃደው ፓርቲም ለመቁጠር እስከሚያስቸግር ተበጣጠሰ ።

እንግዲህ አስቡት ይህ ስብስብ ስልጣን ቢይዝ ሊከተል የሚችለው መዘዝ ልክ «ነበር» በተባለው መጽሐፍ ቁ1 ገጽ 220 - 232 ላይ ሻለቃ ዮሐንስ እንዳደረገው ዓይነት ትዕይንት ይሆን ነበር ። በርግጥ ይህንን ሁሉ ሲደረግ እንደ ኮሎኔል መንግስቱ የመሰለ ተንኮለኛ የሚያልቀውን እስከሚያልቅ ድረስ ብረት ለበስ ውስጥ ሊያደፍጥ ይችል ይሆናል ። ከዚያም ወጥቶ ወንበሩ ላይ ሊቀመጥ ይችል ይሆናል ። ውጤቱ ግን ያው የኮሎኔል መንግስቱ አመራር መሆኑ ነው ። እንደኔ  እንደኔ ያበረው ፓርቲ ጥሬ የቆረጠመ ፓርቲ ቢሆን ኖሮ በዋና ከተማው የተገኘውን ድምጽ በመያዝ ነገም ሌላ ቀን ነውና የተሻለ ውጤት ለማምጣት በሰማላዊ መንገድ መቀጠል ነበረበት ። ግን ምን ያደርጋል የጨረባ ተዝካር አደረጉትና አረፉት ።

እነዚህንና ሌሎች በርካታ ጉዳዮችን እንደ መመዘኛ በመውሰድ ተቃዋሚ ፓርቲዎች መንግስት የሚሆኑበትና አገርና ሕዝብ ለመምራት የሚበቁበት ጊዜ እጅግ በጣም ሩቅ ይመስለኛል ። ገዢው ፓርቲ እስከወድያኛው በስልጣን ይቆይ የሚል ቅዠት ባይኖረኝም ።

ፓርቲዎቹ መንግስት መሆን ማለት እጅግ ከባድ ኃላፊነት መሸከም ማለት እንደሆነ፤በርካታ ተግባራት ተሰርተው ሳይከናወን የቀረ ጉዳይ ስላለ መቃወም ሳይሆን መስራትም ተቃውሞ መቀበልም መሆኑን ተገንዝበው ይህንን ለመሸከም የሚችል ትከሻ ለማዘጋጀት ሌት ተቀን ደፋ ቀና ማለትን ማስቀደም ያለባቸው ይመስለኛል ።

በመሆኑም ስለፈለገ የሚመራ ሳይሆን ኃላፊነት የሚሸከም ተቃዋሚ ፓርቲ እንዲመራን ድምጻችንን የምንሰጥ ከሆነ እንደኔ አስተሳሰብ የፊታችን ምርጫ ብቻ ሳይሆን ቀጣዩም ቀጣዩም የሚታሰብ አይመስለኝም ።ቸር ይግጠመን ።